# የጊዮርጊሱ ግርግር፣ መልካም አዲስ አመት!

(በግርማ ካሳ፣ ቺካጎ)

ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

አዲስ አበባ ጊዮርጊስ አካባቢ ነዉ። ሰዎች በአንድ ቦታ ተከማችተዋል። ግርግር ነገር ይታያል። በመንገድ የሚያልፉ አንድ አባት በመኪና ዉስጥ አብረዋቸዉ ያሉትን «ምንድን ነዉ የተፈጠረዉ?» ይሉና ይጠይቃሉ። ሹፌራቸዉ መኪናዉን ቀስ አድርጎ እንዲያቆም ያዛሉ። ከሹፌሩ ሌላ አብሯቸዉ መኪናዉ ዉስጥ የሚገኝ አንድ ወጣት ከመኪናዉ ወርዶ ፣ ነገሩ ምን እንደሆነ አጣርቶ እንዲመጣ ይልካሉ። ወጣቱ፣ ፈጥኖ ብዙ ሰዎች ወደ ተሰበሰቡበት ያመራል። እየሆነ የየነበረዉን ተመልክቶ ይመለሳል።

አንዲት ድሃ ነፈሰ ጡር ኢትዮጵያዊት ዉሃ ፈሷት፣ ምጧ በድንገት መጥቶ ትሰቃይ ነበር። ይሄዱበት የነበረዉን መኪና አስቁመዉ፣ የተፈጠረዉን ነገር ለማወቅ ወጣቱን የላኩት አባት ደግሞ፣ የልእልት ሳራ ግዛዉ ባለቤት፣ የአጼ ኃይለስላሴ ልጅ፣ ተወዳጁ ልኡል መኮንን ነበሩ።

ልእሉ መኮንን የተፈጠረዉን ጠንቅቀዉ ከተረዱ በኋላ መንገዳችዉን ወደ ቤተ መንግስት አልቀጠሉም። ከኋላቸዉ አጅቦ በሚከተለዉ ሌላ መኪና፣ በአስቸኳይ ኢትዮጵያዊቷ ተጭና ወደ ሆስፒታል እንድትሄድ ያዛሉ። እርሳቸዉ በመኪናቸዉ ይችን መንገድ ላይ የወደቀች ሴት ተከትለዉ ሆስፒታል ድረስ ይጓዛሉ።

ይህ ሲሆን ገና አልተወለድኩም። ስለ ልኡል መኮንን ብዙም አላዉቅም። ነገር ግን ድሃ የሚወዱ፣ በህዝብ በጣም ተወዳጅ እንደነበሩ ብዙ ጊዜ ሰምቼያለሁ። የዚችን  የነፍሰ ጡሯን ሴት ታሪክ ግን በቅርቡ ነበር የሰማሁት። ልቤ በጣም ተነካ። ከአንድ መሪ ማየት የምፈለገዉን ከልኡል መኮንን አየሁ።

ልኡል መኮንን የጊዮርጊሱን ግርግር ባዩ ጊዜ «እኔ የምኖረዉ አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ነዉ፤ ከኔ ጋር የሚገናኝ ነገር የለም። ጊዜዬን በዚህ ድሃ ሴት ዙሪያ ከማጠፋ በቶሎ ወደ ቢትወደድ እንትና ፤ ራስ  እገሌ  .. ጋር መሄዱ ይሻለኛል» ብለዉ መንገዳቸዉ መቀጠል ይችሉ ነበር። ነገር ግን መሪ ማለት፣ የሚመራዉን ህዝብ ችግር የሚያይ፣ የሚያዉቅ፣ መፍትሄም የሚፈልግ መሆኑን የተረዱ ሰዉ ነበሩ።

ልኡል መኮንን በሴቲቱ ላይ የደረሰዉን ችግር በተረዱ ጊዜ ታክሲ እንዲወስዳት ሳንቲም መወርወር ይችሉ ነበር። ነገር ግን መሪ ማለት ለሚመራዉ ሕዝብ የሚያስብ፣ የሚመራዉ ሕዝብን ችግር የራሱ ችግር አድርጎ የሚቆጥር እንደሆነ አዉቀዉ ነበር። በመሆኑም የዚችን ሴት ችግር የራሳቸዉ ችግር አድርገዉ ወሰዱት። መኳንንት በሚሳፈሩበት መኪና፣ ይች ምስኪን ድህ ሴት እስከነ ደሟ እንድተቀመጥ አስደረጉ። የራሳቸዉ ሚስት፣ እህቶች፣ የቅርብ ዘመድ እንደሚንከባከቡት ለዚህ ድህ ሴት እንክብካቤ አደረጉላት። በሰላም ሆስፒታል አደረሷት። ሴቲቱም በሰላም ተገላገለች።

ከ19 አመታት በፊት ነበር። አስመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበርኩኝ ጊዜ መድሃኔ አለም የሚባል የኦርቶዶክ ቤተ ክርስቲያን አምላክን ላመሰግን  እሄዳለሁ። አንድ አባት በዚያ ተቀምጠዋል።

እዚያዉ አስመራ በለመድኩት የተንተባተበ ትግሪኛ ከርሳቸዉ ጋር ጨዋታ ጀመርኩ። በአስመራ ከተማ ስለሚፈነዳዉና ሻእቢያ ከሩቅ ስለሚተኩሰዉ ሚሳዬል (ያኔ ግራፒ ነበር የምንለዉ) አነሳን። ትዝ ይለኛል በሚፈነዳዉ ሚሳዬል ምክንያት ከቴራ ቦሎና አይሮፕላን ማረፊያዉ አካባቢ (ደቡብ አስመራ) ህዝቡ ቅዬዉን እየለቀቀ ወደ መሃልና ሰሜን አስመራ ይፈልስ ነበር። «እንደዉ እግዚአብሄር ሰላምን ያምጣልን። መፍትሄዉ እርሱ ብቻ ነዉ » አልኳቸዉ እኚህን አባት። እርሳቸዉም «ልክ ነህ ፣ ሰላም ነዉ መፍትሄዉ። ከጅምሩ ቀዉሱና ጦርነቱ በሰላም በንግግር ቢፈታ ኖሮ ብዙ ሺህ ወጣት ባልሞተ ነበር» ሲሉ ስለ አንድ ሰዉ አጫወቱኝ፤ ጄነራል አማን አንዶም!

በአብዮቱ ወቅት ነዉ። ጀግናዉና ዝነኛዉ የጦር መኮንን ጄነራል አማን አንዶም የደርግ ሊቀመንበር ሆነዉ ተሾመዋል። በኤርትራ ሻእቢያና ጀበሃ እየበረቱ የመጡበት ጊዜ ነበር። በተለይም በኤርትራ የነበረዉ ፌደረሽን በአጼ ኃይለስላሴ ከፈረሰ ጀምሮ፣ የመገንጠል ጥያቄ ሥር እየሰደደ የመጣበት ወቅት ነበር።

ጄኔራል አማን አንዶም ነፍጥ አንስተዉ የሸፈቱትን አነጋግረዉ እያሳመኑ በኤርትራ የተፈጠረዉን ቀዉስ በንግግር በማሳመን ለመፍታት ትልቅ ጥረት ጀምረዉ ነበር። ኤርትራ የኢትዮጵያ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ አካል እንደሆነች፣ የኢትዮጵያ ስልጣኔ የጀመረዉ ከትግራይና ከኤርትራ እንደሆነ፣ በሰንአፈ ኤርትራ እንደተወለዱት የአክሱሙ ንጉስ ኤዛና ብዙ ታላላቅ የኢትዮጵያ ነገስታት ከኤርትራ ጋር ትስስር እንዳላቸዉ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ከጣሊያኖችና ከግብጾች ጋር በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን (ኤርትራዉያንንም ጨምሮ) ደማቸዉ በኤርትራ ምድር እንደፈሰሰ፣ ከኤርትራ ዉጭ በመቶ ሺሆች የኤርትራ ተወላጆች ኢትዮጵያ ዉስጥ፣ በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ከተቀረዉ የኢትዮጵያ ክፍል የመጡ በኤርትራ ዉስጥ እንደሚኖሩ፣ ህዝቡ እንደተደባለቀና እንደተዛመደ እያስረዱ ሻእቢያና ጀብሃ የመገንጠል ጥያቄያቸዉን ትተዉ ወደ ሰላም እንዲመጡ እያሳመኑ ነበር።

አዲስ አበባ የተቀመጡት፣ አርቆ ማስተዋል የተሳናቸዉ፣ በግርግር ስልጣን የጨበጡትና ትንሽ እዉቀት ይዘዉ የሚንጠራሩ መቶ አለቆች፣ የሰላሙን ጥረት ቀጩት። የትላንቱ ጀግንነት ተረስቶ፣ የትላንቱ ጥሩ ሥራ አመድ ለብሶ፣ በትግሪኛ ህዝቡን ማናገራቸዉ እንደ ሐጢያትና ወንጀል ተቆጥሮ ጄኔራል አማን አንዶም «የወንበዴ ረዳት» ተደርገዉ ተወሰዱ። አዲስ አበባ አይሮፕላን ማረፊያ በሚገኘዉ ቤታቸዉ በግፍና በጭካኔ ተገደሉ።

ጦርነት ከተፈለገ በኢትዮጵያ ታሪክ ነበሩ ከሚባሉ ታላቅ የጦር መሪ አንዱ ጄኔራል አማን አንዶም ነበሩ። ጦር መርቶ፣ በጦርነት ድል ማድረግ የለመዱና የሚችሉ የወታደራዊ አመራር ብቃት የተላበሱ ነበሩ። ነገር ግን፣ በተለይም የራስን ወገን በጠመንጃና በመድፍ ከማስፈራራት እንዲሁም በጉልበትና በጡንቻ ሕዝብን ከማስገበር ይልቅ፣ ትሁት ሆኖ በንግግርና በማሳመን የሚገኝ ዉጤት ዘለቄታ ያለዉ መሆኑን የተረዱ ሰዉ ነበሩ። «ጠመንጃ ያነሳዉን ብትገድለዉ ነገ ልጁ ደግሞ ይነሳባሃል። ጠመንጃ ያነሳዉን ግን አሳምነህ ወዳጅ ብታደርግዉ ነገ ልጁ የልጅ ልጁ ወደጆችህ ይሆናሉ» በሚል እምነት ነበር ያኔ በሰላሙ ሃሳብ የተንቀሳቀሱት።

የልኡል መኮንን እና የጄነራል አማን አንዶምን ምሳሌ ያለ ምክንያት አላመጣሁም። አገራችን ኢትዮጵያ ለአመታት ያጣችዉና የጎደላት ነገር ቢኖር እንደዚህ አይነት መሪዎችን ነዉ።

በአሁኑ ጊዜ የትኛዉ የአገራችን መሪ ይሆን ለተጠቃዉ፣ ለተጎዳዉ፣ በግፍ ቀንበር ለሚሰቃየዉ ወገናችን የሚቆረቆረዉ ? የትኛዉ መሪ ይሆን ፍትህ ለተነፈጉት፣ ወንጀል ሳይሰሩ በየእሥር ቤቱ

ለሚማቅቁት ወገኖች የሚያስበዉ ? የትኛዉ መሪ ይሆን ከሼራተን፣ ከቤተ መንግስት፣ በቦሌ መንገድ ካሉ ዳንኪራ ቦታዎች፣ በየቦታዉ ከተሰሩ የታጠሩ የሃብታም ሰፈሮች ወጥቶ ሴቲቱን ለመርዳት መኪናዉን የሚያቆመዉ ?

እንደዉም እንዳየነዉ ከሆኑ፣ የኑሮ ዉድነት በአንድ በኩል እያሰቃየዉ፣ በሌላ በኩል ለሕዝባችን በሽታ የሆኑበት አገርን እንመራለን ብለዉ ስልጣን ላይ የተቀመጡት መሪዎቹ እራሳቸዉ አይደሉምን? ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ጽ/ቤት የተዘረጋዉ የስልጣን መረብ፣  ህዝቡ በፍርሃትና በሰቀቀን አንገቱን ደፍቶ «እሺህ ጌታዬ» ብሎ በአገሩ እንደ ባርያና ሁለተኛ ዜጋ እንዲኖር አልተደረገምን?   የሙስናና የሌብነትን ሌላዉ መረብ ከላይ ወደ ታች በመዘርጋት ህዝቡን  እያስጨነቁት ያሉት አገርን እንመራለን የሚሉቱ አይደሉምን ? ከአሁን ለአሁን ለስልጣናችን ያሰጋናል በማለት ለሰላም፣ ለፍትህ የቆሙትን የሚያስሩና የሚያስቃዩ የሚገድሉም እነዚሁ አገርን እንመራለን የሚሉት አይደሉምን ?

ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ የት ነዉ ያሉት ? አንድ ሰዉ ተኩሰዉ ገድለዋል ? አምስት ሳንቲም ከሰዉ ኪስ ሰርቀዋል? በሕክምና ሞያቸዉ ቀዶ ጥገና ሲያደርጉ መቀስ ሆድ ዉስጥ ረስተዋል ? የአሁኑ የአገራችን ጠቅላይ ሚኒስተር በፓርላማ ሲናገሩ እንደሰማነዉ፣  «ሌቦች፣ ወራዳች...» ብለዉ ተሳድበዋል ? እስቲ የሚደፍር ካለ ይንገረን ...እሥር ቤት እያሉ በበረታባቸዉ ሕመም ምክንያት እስኪሞቱ ድረስ ለዚያ ሁሉ አመታት በእሥር እንዲሰቃዩ መደረጋቸዉ ምን ወንጀል ቢፈጽሙ ነዉ ?

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የት ነዉ ያለችዉ ? ቱሃንና አይጥ በሚሯሯጡበት ቃሊት እሥር ቤት አይደለምን ? ምንድን ነዉ ወንጀሏ ? ዳኛ የነበረች ጊዜ ጉቦ በላች ? በዉጭ አገር ጉብኝት ባደረገች ጊዜ ጦርነት አወጀች ? የአገር ባለስልጣናትን ሰደበች ? ገንዘብ ሰረቀች ? ሕገ መንግስቱን አልቀበልም አለች ? «ይቅርታ ጠይቃ ፣ ይቅርታ አልጠየኩም ብላለች፤ አጭበርበራለች» ይላሉ አቶ መለስ። በርግጥስ ብርቱካን ሚደቅሳ ይቅርታ አልጠየኩም ብላለች ? እንደዉም ቃሌ በተሰኘዉ ጽሁፏ በአገር ሽምግልና ወግ መሰረት «ሕዝብንና መንግስትን  ይቅርታ መጠየቄን አልክድም» አይደለምን ያለችዉ ?

ታዲያ ይሄ ሁሉ የሚያሳየዉ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ባሉ መሪዎች ዘንድ የምናየዉ የልኡል መኮንን አይነት ሃዘኔታን፣ ፍቅርን፣ ርህራሄን፣ ሰላምን፣ በጎነትን  ሳይሆን ጭካኔን፣ ክፋትትን፣ አረመኔነትን አይደለምን?

ከላይ እንደጠቀስኩት ጄነራል አማን አንዶም ጠመንጃ ካነሱ ጋር ያለ ቅድመ ሁኔታ ለመነጋገር ደፈረዉ ነበር። ጠመንጃ ያነሳዉ ጠመንጃዉን ካስቀመጠማ ምን ንግግር ይባላል። «እምቢ አሻፈረኝ ብሎ የሸፈተንስ ጠመንጃህን አስቀምጥና እንነጋገር » ቢባል ከወዲሁ በጠመንጃ ካልተሸነፈ በቀር እሺ ሊል አይችልም።

አቶ መለስ በቅርቡ ለሰላም እንደቆሙ ገልጸዉልናል። ከግንቦት ሰባትና ከኦነግ ጋር ለመነጋገር ፍቃደኝነታቸዉ አሳዉቀዋል። «በሕግ መንግስቱ አምነዉ ፤ ሕገ መንግስቱን ለመከተል ፍቃደኛ እስከሆኑና በሰላም ለመታገል(ጠመንጃቸዉን ለማስቀመጥ) እስከወሰኑ ድረስ» እነ ኦነግ አገር ዉስጥ መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ነዉ የጠቁሙት።

መቼም የሰላም ሃሳብን የሚጠላ የለም። ከማንም የምጣ፣ ማንኛዉም የሰላምና የእርቅ ሃሳብ የሚደገፍ ነዉ።፡ነገር ግን ይህ የአቶ መለስ የሰላም ሃሳብ፣ ገና ከአቶ መለስ አንደበት እንደወጣ

ያኔዉኑ፣ እራሳቸዉ አቶ መለስ በተግባራቸዉ ሽረዉታል። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ትፈታለች ወይ ተብለዉ ሲጠየቁ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይ የሕግ ጉዳይ እንደሆነ ነበር የገለጹት።

እንዴት ተደረጎ ነዉ ታዲያ በሰላም የሚታገሉትን እያሰሩ፣ በዉጭ ያለዉንና ነፍጥ ያነሳዉን ተቃዋሚ፣ አቶ መለስ ዜናዊን አምኖ ነፍጡን የሚያስቀምጠዉ? እንዴት ተደረጎ ነዉ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ቃሊቲ እየማቀቀች፣ በሰላም ይታገሉ የነበሩት እንደ አቶ በቀለ ጂራታ ከአገር እንዲሰደዱ እየተደረገ፣ የአነጉ አቶ ዳዎድ ኢብሳ ወይንም የግንቦት ሰባቱ ዶር ብርሃኑ ነጋ፣ የአቶ መለስን የሰላም ጥሪ አክብረዉ በሰላም ለመታገል አገር ቤት የሚገቡት ?

እንግዲህ አቶ መለስና ጓዶቻቸዉ በርግጥ ለሕዝብ እናስባለን፣ ለድሃ እንቆረቆራለን የሚሉ ከሆነ ፣ በአገራችን ሰላም እንዲሰፍን በርግጥ ፍላጎት ካላቸዉ፣ በሥራቸዉ ያሳዩን። ፈረንጆቹ «ዌር ኢዝ ዘሚት» እንደሚሉት ወሬዉና ጩኸቱ፣ ጋዜጣዊዉ መግለጫ ይብቃና በፖሊሲና በተግባር የተጨበጠ ነገር ያሳዩን።

የፊታችን አዲስ አመት መልካም አጋጣሚዎች ከፍቶላቸዋል። ካሉበት አጥር ወጣ ብለዉ የጊዮርጊስን ግርግር መመልከት ይኖርባቸዋል። በሰላዮቻቸው ፊት ሳይሆን በጓዳ በሕዝብ ዘንድ የሚነገረዉን ማዳመጥ መቻል አለባቸዉ። የሕዝብን ልብ ትረታ የያዘችዉን ዳግማዊት ጣይቱ ብጡል ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በአስቸኳይ መፍታት ይኖርባቸዋል። የልኡል መኮንን አይነት ርህራሄና የድሃ ፍቅር ልባቸዉን ሊሞላ ይገባል። ጄነራል አማን አንዶም ጦራቸዉን ወደ ሰገባዉ ከተዉ በንግግርና በዉይይት በወንድማማቾች መካከል የተፈጠረዉን ቀዉስ ለመፍታት እንደሞከሩት ሁሉ፣ እነርሱም በሕዝቡ ላይ የጫኑትን የፍርሃትና የጭቆና፣ የጡንቻ የጉልበት አገዛዝ አቁመዉ፣ እራሳቸዉን በሕዝብና በታላቁ እግዚአብሄር ፊት አዋርደዉ፣ የሰላም የወንድማማችነት፣ የመከባበር ባህል እንዲሰፍ ጉልህ እርምጃ መዉሰድ ይጠበቅባችዋል።

ላለፉት አመታት የተመኘነዉና ተስፋ ያደረግነዉ አልሆነልንም። በደስታ አመቱን ጀምረን በሃዘን ነዉ ያጠናቀቅነዉ። የ2002 አመትን ከጥቂት ቀናት በኋላ እንሰናበተዋለን። እንደ 2002 እና ያለፉት አመታትስ 2003 ዓ ምን አያደርግብን ! በዚህ አዲስ አመት እግዚአብሄር ቸሩን ያሰማን !

መልካም አዲስ አመት !

---

muziky68@yahoo.com